ተግባርን ሓላፍነትን ኣብያተ ምኽርን ፈፀምቲ ኣካላትን ንምቕፃል፣ ንምምሕያሽን ፣ ንምጥንኻርን ዝወፀ ደንቢ ቁፅሪ 21/2017 ዓ/ም

ብውዕሊ ሰላም ፕሪቶርያ ዓንቀፅ 10/1/፣ ፌደራል ኣዋጅ ቁፅሪ 359/1995 ዓንቀፅ 15ን ሰዓብቱን፣ ደንቢ ቁፅሪ 533/2015ን መሰረት ግዝያዊ ምምሕዳር ክልል ትግራይ ተጣይሹ ኣብ ስራሕ ዘሎ ብምኻኑ፣

ብመሰረት ፌደራል ኣዋጅ ቁፅሪ 359/1995 ዓንቀፅ 14/3-ለ/፣15/2-ሐ/ መሰረት ሕግን ስርዓትን ክኽበርን ኣድላይ ስጉምቲ ብምውሳድ ፀጥታን ሰላምን ውሑስ ንምግባር ግዝያዊ ምምሕዳር ክልል ትግራይ ዘለዎ ግቡእን ሓላፍነት ብኣግባቡ ንምፍፃም ኣድላይ ኮይኑ ስለዝተረኸበ፣

ግዝያዊ ምምሕዳር ክልል ትግራይ ብሕጊ ዝተውሃቦ ስልጣንን ተግባርን ኣብ ምፍፃም ዘጋጥሙ ዘለዉ ፀገማት ብምፍታሕ ውዕሊ ሰላም ፕሪቶርያ ብዘይተሸራረፈ መንገዲ ምፍፃም ወሳኒ ብምኻኑን ኣብ መሓውር መንግስትን ህዝብን ዝርአ ዘሎ ሰንፈላልን ዘይምርግጋእን ብምፍታሕ ዝሰኸነ ናይ ምምራሕን ምስራሕን መንፈስ ምፍጣር

የምክር ቤቶች እና አስፈፃሚ አካላት ተግባር እና ሓላፊነት ለማስቀጠል ፣ ለማሻሻል እንዲሁም ለማጠናከር የወጣ ደንብ ቁጥር 21/ 2017 ዓ/ም

በፕሪቶሪያ የሰላም ውል ዓንቀፅ 10/1/፣ የፌደራል አዋጅ ቁጥር 359/1995 ዓንቀፅ 15 እና ተከታዮቹ ዓንቀፆች እንዲሁም ደንብ ቁጥር 533/2015 መሰረት የትግራይ ክልል ግዝያዊ አስተዳደር የተቋቋመ በመሆኑ፣

የፌደራል መንግስት ባወጣው አዋጅ ቁጥር 359/1995 ዓንቀፅ 14/3-ለ/፣15/2-ሐ/ መሰረት ሕግ እና ስርዓት እንዲከበር አስፈላጊውን እርምጃ በመውሰድ ሰላም እና ፀጥታ እንዲረጋገጥ ለማድረግ የትግራይ ክልል ግዝያዊ አስተዳደር የተጣለበትን ግዴታ እና ሓላፊነት በአግባቡ ለመፈፀም አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ፣

የትግራይ ክልል ግዝያዊ አስተዳደር በሕግ የተሰጠውን ስልጣን እና ተግባር በመፈፀም ረገድ እያጋጠሙት ያሉ ችግሮችን በመፍታት የፕሪቶሪያ የሰላም ውል ስምምነት ሳይሸራረፍ ለመፈፀም ወሳኝ በመሆኑ በመንግስት መዋቅር እና ሕዝብ ዘንድ እየታየ ያለው መጉላላት እና አለመረጋጋት በመፍታት የሰከነ የአመራር እና የአሰራር

ኣገዳሲ ብምዃኑ፣

ስራሕን ሓላፍነትን በብብርኩ ዝርከቡ ኣብያተ ምኽሪን ፈፀምቲ ኣካላትን ምስ ተግባርን ሓላፍነትን ግዝያዊ ምምሕዳር ክልል ትግራይ ምጥዕዓም ስለዘድሊ፣

ኣብ 2012 ዓ/ም ብዝተገበረ ናይ ወረዳን ከተማን ምትዕርራይ ኣብ 2005 ዓ/ም መረፃ ኣብ ዝተገበረሉ እዋን ብሕጋዊ መረፃ ሕጋዊ ኣፍልጦ ረኺቦም ብሕጋዊ ኣገባብ ዝተጣየሹ ኣብያተ ምኽሪ ናብ ክልተን ልዕሊኡን ተመቓቒሎም ናይ ህዝቢ መረፃ መሰረት ዝገበረ ሕጋዊ ሰውነቶም ስለዝሰኣኑ፣ ብዕድመ፣ ሞት፣ ምፍንቓላትን ካልኦት ምኽንያታትን ኣባላቶም ብምጉዳሎም ዝተማልአ ቁመና ከይህልዎም ዝገበረ ብምዃኑ፣

ተሳትፎ ዝተፈላለዩ ፖለቲካዊ ውድባት፣ መናእሰይ፣ ደቂኣንስትዮን ዝተፈላለዩ ክፋላት ሕብረተሰብን ሓቛፊ ብዝኾነ ኣገባብ መሰል ህዝቢ ዘረጋግፅሉን፣ ዝጎደሉ ኣብያተ ምኽሪ ብቐጥታዊ ተሳትፎ ህዝቢ ዝማልኡሉን ነፃነቶም ሓልዮም ዝሰርሑሉን ኩነታት ምፍጣር ኣገዳሲ ብምዃኑ፣

መንፈስ መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ ፤

በየደረጃው የሚገኙ ምክር ቤቶች እና አስፈፃሚ አካላት ሥራ እና ሓላፊነታቸው ከትግራይ ክልል ግዝያዊ አስተዳደር ተግባር እና ሓላፊነት ጋር ማጣጣም ስለሚያስፈልግ፤

በ2012 ዓ/ም የተደረገ የወረዳዎች እና ከተሞች ዳግም ማደራጀት በ2005 ዓ/ም በተካሄደው ምርጫ ወቅት በሕጋዊ ምርጫ ሕጋዊ እውቅና አግኝተው በሕጋዊ መንገድ የተቋቋሙ ምክር ቤቶች ወደ ሁለት እና ከዚያም በላይ ተከፋፍለው በሕዝብ ምርጫ ላይ የተመሰረተ ሕጋዊ ሰውነታቸው ስላጡ፤ በዕድሜ፤ በሞት፤ መፈናቀል እና ሌሎች ምክንያቶች ብዙዎች አባሎቻቸው የተጓደሉ ያልተሟላ የምክር ቤት አባላት እንዲኖራቸው በማድረግ የተሟላ ቁመና እንዳይኖራቸው ያደረገ በመሆኑ፤

የተለያዩ ፖለቲካዊ ድርጅቶች፤ ወጣቶች፤ ሴቶች እና ልዩልዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ተሳትፎ አካታች በሆነ አግባብ የሕዝቦች መብት የሚረጋገጥበት ፤ ያልተሟሉ የምክር ቤት አባላት በቀጥታዊ የሕዝብ ተሳትፎ የሚሟሉበትና ነፃነታቸው ጠብቀው የሚሰሩበትን ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፤

ኣብ ቀረባ እዋን ኣብያተ ምኽሪ ተጠቒምካ ዝግበር ዘሎ ዘይምኽኑይን ዘይሕጋውን ምሻምን ምስዓርን ዝፈጥር ዘሎ ማሕበረ ኢኮኖሚያዊን ፖለቲካዊን ፀገማትን ናይ ፀጥታ ክፍተትን ስግኣትን እናተበራኸተ ዝኸይድ ዘሎ ብምዃኑ ነዚ ምእላይ ኣገዳሲ ብምዃኑ፣

በቲ ብርኡ ዝርከቡ ኣብያተ ምኽሪ ብመሰረት ሕገ መንግስቲ ዝተውሃቦም ግልጋሎት ዘበን ስራሕ ዝወድኡን ሕጋዊ መሰረቶም ዘብቀዐ ብምዃኑ ኣብዚ ሐዚ እዋን ብቐጥታ መረፃ ፍቓድ ህዝቢ ዝረኸበ ብሕገመንግስቲ መሰረት ሕጋዊ ስልጣን ዘለዎ ቤት ምኽሪ ዘየለ ብምዃኑ፣

እዋናዊ ብምብቃዑ ክፈርሱ ክይኮነስ ሕጋውነት ዘላብሰን ዘለዎም ፀገማት ብዝፈትሕን ኣግባብ ተጠናኺሮም ክቕፅሉን ቀፃሊ መረፃ ክሳብ ዝካየድ ኣካል ግዚያዊ ምምሕዳር ኮይኖም ናብ ቀፃሊ መረፃ ዘሰጋግር ስራሕቲ ክሰርሑን ናይ ህዝቢ ድምፂ ክኾኑን ዘኽእሎም ኣብ ተግባርን ሓላፍነትን ምምሕያሽን ምጥንኻርን ኣድላዪ ኮይኑ ስለዝተረኸበ፣

ካቢኔ ግዚያዊ ምምሕዳር ክልል ትግራይ ብመሰረት ፈደራል ኣዋጅ ቁፅሪ

ከቅርብ ግዜ ወዲህ ምክር ቤቶችን በመጠቀም እየተካሄደ ያለው ምክንያት አልባ እና ሕገወጥ መሾም እና ማንሳት እየፈጠረ ያለው የማሕበረ ኢኮኖሚ እና የፖለቲካ እንዲሁም የፀጥታ ችግር፣ ክፍተት እና ስጋት እየተበራከተ እየሄደ ያለ በመሆኑና ይህንን ማስወገድ አስፈላጊ በመሆኑ፣

በየደረጃው የሚገኙ ምክር ቤቶች በሕገ መንግስት መሰረት የተሰጣቸው የሥራ ዘመናቸው የጨረሱ እና የሕግ መሰረታቸው ያበቃ በመሆኑ በአሁኑ ወቅት በቀጥታ የሕዝብ ፍቃድ ያገኘ በሕገ መንግስት መሰረት ሕጋዊ ስልጣን ያለው ምክር ቤት የሌለ በመሆኑ፣

የሥራ ዘመናቸው በማብቃቱ የተነሳ እንዲፈርሱ ሳይሆን ሕጋዊነት በማላበስ ያሉባቸው ችግሮች በሚፈታ መንገድ ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ቀጣይ ምርጫ እስከሚካሄድ ድረስ የግዚያዊ መስተዳደሩ አካል ሁነው ወደ ቀጣይ ምርጫ የሚያሸጋግር ሥራዎች በመሥራት እና የሕዝብ ድምፅ ሊሆኑ የሚያስችላቸውን ተግባር እና ሓላፊነታቸው ማሻሻል እንዲሁም ማጠናከር አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ፣

የትግራይ ክልል ግዚያዊ አስተዳደር ካቢኔ በፌደራል አዋጅ ቁጥር 359/1995 ዓንቀፅ

359/1995 ዓንቀፅ 15፣ ከምኡውን ብደንቢ ቁፅሪ 533/2015 ዓንቀፅ 5 እዚ ደንቢ አውፂኡ አሎ።

ዓንቀፅ 1. ሓፂር ርእሲ

እዚ ደንቢ ተግባርን ሓላፍነትን ኣብያተ ምኽርን ፈፀምቲ ኣካላትን ንምቕያል፣ ንምምሕያሽን ንምውንኻርን ዝወፀ ደንቢ ቁፅሪ 21/2017 ዓ/ም ተባሂሉ ክጥቀስ ይኽእል።

ዓንቀፅ 2. ትርጉም፦

ኣብዚ ደንቢ

1. "ክልል " ማለት ክልል ትግራይ እዩ፤
2. "ግዝያዊ ምምሕዳር " ማለት ግዝያዊ ምምሕዳር ክልል ትግራይ እዩ፤
3. "ካቢኔ ግዝያዊ ምምሕዳር" ማለት ካቢኔ ግዝያዊ ምምሕዳር ክልል ትግራይ እዩ፤
4. "ርእሰ ምምሕዳር " ማለት ርእሰ ምምሕዳር ግዝያዊ ምምሕዳር ክልል ትግራይ እዩ፤
5. "መሓውር መንግስቲ" ማለት ካብ ላዕሊ ክሳብ ታሕቲ ኣብ ዝርከብ

15፣እንዲሁም በደንብ ቁጥር 533/2015 ዓንቀፅ 5 መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

ዓንቀፅ 1. አጭር ርእስ

ይህ ደንብ " የምክር ቤቶች እና አስፈፃሚ አካላት ተግባር እና ሓላፊነት ለማስተጠል፣ ለማሻሻል እንዲሁም ለማጠናከር የወጣ ደንብ ቁጥር 21/2017 ዓ/ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

ዓንቀፅ 2 ትርጉም፦

በዚህ ደንብ

1. "ክልል " ማለት የትግራይ ክልል ነው።
2. "ግዝያዊ አስተዳደር" ማለት የትግራይ ክልል ግዝያዊ አስተዳደር ነው፤
3. "የግዝያዊ አስተዳደር ካቢኔ " ማለት የትግራይ ክልል ግዝያዊ አስተዳደር ካቢኔ ነው ።
4. "ርእሰ መስተዳደር" ማለት የትግራይ ክልል ግዝያዊ አስተዳደር ርእሰ መስተዳድር ነው።
5. "የመንግስት መዋቅር" ማለት ከላይ እስከ ታች የሚገኙ የመንግስት መዋቅር

መሓውር መንግስቲ ክይኑ ኣብ ጣብያ፣ ወረዳ፣ ከተማ፣ ክፍለ ከተማ፣ ምምሕዳር ከተማ መቐለ፣ ዞባ ከነ ክልል ዝርከቡ መሓውር መንግስቲ ይሓውስ።

6. "ኣብያተ ምኽሪ" ማለት ኣብያተ ምኽሪ ምምሕዳር ከተማ መቐለ፣ ከተማ፣ ክ/ከተማ፣ ናይ ወረዳን ጣብያን ኣብያተ ምኽሪ ዘካተተ እዩ፤

7. "ኮሚቴ ፈፃሚ ስራሕ" ወይ "ኮሚቴ ክንቲባ" ማለት ኮሚቴ ፈፃሚ ስራሕ ወረዳ ወይ ክ/ከተማ ወይ ጣብያን ከም ኣግባብነቱ ኮሚቴ ክንቲባ ምምሕዳር ከተማ መቐለን ካልኦት ከተማታትን ዝሓዉስ እዩ፤

8. "ኮሚቴ ምምሕዳር ዞባ" ማለት ብምምሕዳር ክልል ዝቖመ ንዞባ ናይ ምምሕዳር ስልጣን ዝተውሃቦ ፈፃሚ ሕጊ እዩ፤

9. "ፈፀምቲ ኣካላት" ማለት ካብ ጣብያ ክሳብ ክልል ዘለዉ ፈፀምቲ ስራሕ ዘጠቓልል እዩ፤

10. "ዋና ኣመሓዳሪ" ወይ"ምክትል ዋና ኣመሓዳሪ" ማለት ዋና ኣመሓዳሪ ወይ ምክትል ዋና ኣመሓዳሪ ወረዳ፣

ሆኖ በቀበሌ፣ ወረዳ፣ ከተማ፣ ክፍለ ከተማ፣ የመቐለ ከተማ አስተዳደር፣ ዞን ሆነ በክልል የሚገኙ የመንግስት መዋቅርን ይጨምራል፣

6. "ምክር ቤቶች" ማለት የመቐለ ከተማ አስተዳደር፣ ከተማ፣ ክፍለ ከተማ ፣ ወረዳ እና የቀበሌ ምክር ቤቶችን ያካተተ ነው።

7. "የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ""ወይም የከንቲባ ኮሚቴ" ማለት የወረዳ፣ ወይም ክፍለ ከተማ፣ ወይም የቀበሌ፤ እንደ አግባብነቱ የመቐለ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ እና የሌሎች ከተሞች ከንቲባ ኮሚቴዎችን ያጠቃለለ ነው፣

8. "የዞን አስተዳደር ኮሚቴ" ማለት በክልል መስተዳደር የተቋቋመ ለዞን የማስተዳደር ስልጣን የተሰጠው የሕግ አስፈፃሚ ነው፣

9. "አስፈፃሚ አካላት" ማለት ከቀበሌ እስከ ክልል ያሉት የሥራ አስፈፃሚ ያጠቃለለ ነው።

10. "ዋና አስተዳዳሪ"ወይም "ምክትል ዋና አስተዳዳሪ" ማለት ዋና አስተዳዳሪ ወይም ምክትል አስተዳዳሪ፣ ወረዳ፣

ከ/ከተማን ማብያን ዘጠቓልል እዩ፤

11. "ከንቲባ" ወይ "ምክትል ከንቲባ" ማለት ከንቲባ ወይ ምክትል ከንቲባ ምምሕዳር ከተማ መቐለን ካልኦት ከተማታትን ዘጠቓልል ኮይኑ ዋና መራሒ ስራሕ ከተማን ነቲ ከንቲባ ተኪኡ ዝሰርሕ ምክትል ከንቲባን ዝሓውስ እዩ፤

12. "ሽመት" ማለት ብሕጊ መሰረት ብዝምልከቶ ኣካል ዝወሃብ ሹመት እዩ፤

13. "ሰብ" ማለት ተፈጥሮኣዊ ሰብ ወይ ብሕጊ መሰል ሰብነት ዝተውሃቦ ኣካል እዩ።

**ዓንቀፅ 3. ኣገላልፃ ፆታ**

ኣብዚ ደንቢ ብተባዕታይ ፆታ ዝተገለፀ ንኣንስታይ ፆታ እውን ዝሓውስ እዩ።

**ዓንቀፅ 4. ዕላማ**

1. ዝርአ ዘሎ ፀገም ፀጥታን ስርዓት ኣልቦነትን ብምውጋድ ልዕልነት ሕግን ሕገመንግስታዊ ስርዓትን እዚ ክልል ክረጋገፅ ምግባር፣
2. ብመንግስቲ ዝካየዱ መደባት ዝተወደቡ፣ ዝተናበቡ፣ ዝተማእኸሉ፣ ሕግን መስርሕን ዝተኸተሉ ንምግባር፣

ክፍለ ከተማና፣ ቀበሌ ያጠቃልላል።

11. "ከንቲባ" ወይም "ምክትል ከንቲባ" ማለት የመቐለ ከተማ አስተዳደር እና የሌሎች ከተሞች ከንቲባ ወይ ምክትል ከንቲባ ያጠቃለለ ሆኖ የከተማው ዋና የሥራ መሪ እና ከንቲባውን ተክቶ የሚሰራ ምክትል ከንቲባን ያካተተ ነው።

12. "ሹመት" ማለት በሕግ መሰረት በሚመለከተው አካል የተሰጠ ሹመት ነው።

13. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ ሕጋዊ ሰውነት የተሰጠው አካል ነው።

**ዓንቀፅ 3. የፆታ አገላለፅ**

በዚህ ደንብ በወንድ ፆታ የተገለፀ ለሴት ፆታም ይጨምራል፣

**ዓንቀፅ 4. ዓላማ**

1. እየታየ ያለው የፀጥታ ችግር ስርዓት አልበኝነትን በማስወገድ የክልሉ የሕግ የበላይነት እና ሕገ መንግስታዊ ስርዓት እንዲረጋገጥ ማድረግ፣
2. በመንግስት የሚካሄዱ ሥራዎች፣ የተቀናጁ፣ የተናበቡና የተማከሉ በማድረግ ሕግ እና አሰራር የተከተሉ ለማድረግ፣



Tigray Regional State Interim Administratio
CamScanner

3. ኣብ ተግባር ብጭብጥ የጋጥሙ ዘለዉ ስራሕቲ መንግስቲ ናይ ምትዕንቓፍ ተግባራት ተኣሪሞም መሓወሪ መንግስቲ ስራሕቲ በቲ ብሕጊ ዝተውሃቦ ስልጣንን ሓላፍነትን መሰረት ብኣግባቡ ክፍፅምን ክፈፅምን ንምግባር፣

4. ብኸንቲ ሃፍቲ ህዝብን መንግስትን ብምውጋድ ናብ ስርዓት ብምእታው ብመስርሕ ክተሓዝን ኣብ ጥቕሚ ክውዕልን ምግባር፣

## ዓንቀፅ 5. ምቕፃል ኣብያተ ምኽርን ፈፀምቲ ኣካላትን፦

ግዚኦም ወዲኦም ሕጋዊ ስልጣኖም ኣብቂዑ ግን ድማ ኣብ ስራሕ ዘለዉ ኣብያተ ምኽርን ፈፀምቲ ኣካላትን ኣካል ግዝያዊ ምምሕዳር ኮይኖም ቀፃሊ መረፃ ክሳብ ዝካየድ ናይ ስግግር ስራሕቲ እናሰርሑ በዚ ደንቢ ብዝተቐመጠ መሰረት ይቕፅሉ።

## ዓንቀፅ 6. ተግባርን ሓላፍነትን ኣብያተ ምኽርን ፈፀምቲ ኣካላትን

1. ኣብያተ ምኽሪን ፈፀምቲ ኣካላትን ብመሰረት ሕገመንግስቲ ትግራይን መመሓየሺኡን ካልኦት ሕግታትን ዝተውሃቦም ተግባርን ሓላፍነትን ይህልዎም።

3. በተግባር በተጨባጭ ሁኔታ እያጋጠሙ ያሉት የመንግስት ሥራዎች የሚያደናቀፍ እንቅሳቃሴዎች ታርመው የመንግስት መዋቅር ሥራዎቹ በሕግ በተሰጠው ስልጣን እና ሓላፊነት መሰረት በአግባቡ እንዲፈፀም እና እንዲያስፈፅም ለማድረግ፣

4. የሕዝብ እና መንግስት ሀብት ብክነት በማስወገድ በስርዓትና አሰራር መሰረት እንዲያዝና ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ፣

## ዓንቀፅ 5. ምክር ቤቶች እና አስፈፃሚ አካላት ስለማስቀጠል፦

ግዝያቸው ጨርሰው ሕጋዊ ስልጣናቸው አብቅቶ እያለ በሥራ ላይ ያሉ ምክር ቤቶች እና አስፈፃሚ አካላት የግዝያዊ አስተዳደር አካል ሁነው ቀጣይ ምርጫ እስኪካሄድ ድረስ የሽግግር ሥራዎች እየሰሩ በዚህ ደንብ በተተመጠው መሰረት ይቀጥላሉ።

## ዓንቀፅ 6.የምክር ቤቶች እና አስፈፃሚ አካላት ተግባር እና ሓላፊነት

1. ምክር ቤቶች እና አስፈፃሚ አካላት በትግራይ ሕገ መንግስት ከነማሻሻያው እንዲሁም በሌሎች ሕጎች የተሰጣቸው ተግባር እና ሓላፊነት ይኖራቸዋል።

2. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 ዝተደንገገ ከምዘሎ ኮይኑ ኣብያተ ምኽሪ ዝስዕቡ ተግባርን ሓላፍነትን ይህልውዎም።

ሀ. ናይ ግዝያዊ ምምሕዳር ስልጣንን ሓላፍነትን ናይ ምኽባርን ከኽበር ናይ ምግባርን፣

ለ. ዘውፅእዎ ትልምን ዝፍፅምዎም ተግባርን ምስ ትልምን ተግባርን ግዝያዊ ምምሕዳር ከጠዓዓም ምግባር፣

ሐ. ግዝያዊ ምምሕዳር ዳግመ ህንፀትን ቀፃሊ መረፃ ንምክያድን ዘውፅእም ፕሮግራማት፣ ውሳኔታት፣ መምርሒታትን ትእዛዛትን ተቐቢሎም ሙሉእ ብሙሉእ ናይ ምፍፃም፣

መ. ብግዝያዊ ምምሕዳር ዝግበሩ ናይ ኣመራርሓ ምትዕርራያት ተቐቢሎም ኣብ ተግባር ከውዕል ይሰርሑ፣

ረ. ኣፈ-ጉባኤን ምክትል ኣፈ-ጉባኤን ኣብያተ ምኽሪ መደባት ግዝያዊ ምምሕዳር ተኸታቲሎም ናይ ምፍፃምን ከፈፀሙ ምግባርን ግቡእን ሓላፍነትን ኣለዎም።

2. በዚህ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 የተደነገገው እንዳለ ሆኖ ምክር ቤቶች የሚከተሉትን ተግባር እና ሓላፊነት ይኖራቸዋል።

ሀ.የግዝያዊ አስተዳደር ስልጣን እና ሓላፊነት የማክበርና እንዲከበር የማድረግ፣

ለ.የሚያወጡት እቅድ እና የሚፈፅሙት ተግባር ከግዝያዊ አስተዳደር እቅድ እና ተግባር የተጣጣመ ማድረግ፣

ሐ. ግዝያዊ አስተዳደር ዳግመ ግንባታ እና ቀጣይ ምርጫ ለማካሄድ በሚያወጣቸው ፕሮግራሞች፣ ውሳኔዎች፣ መምሪያዎችና ትእዛዞች ተቀብለው ሙሉ በሙሉ የመፈፀም፣

መ. በግዝያዊ አስተዳደር የሚፈፀሙ የአመራር ማደራጀቶች ተቀብለው እንዲተገበር ይሰራሉ፣

ረ. የምክር ቤቶች አፈ -ጉባኤዎች እና ምክትል አፈ-ጉባኤዎች የግዝያዊ አስተዳደር ሥራዎች ተከትለው የመፈፀም እና የማስፈፀም ግዴታና ሓላፊነት አላቸው።

3. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 ዝተደንገገ እንተሃለወ እውን፡-

ሀ. ርእሰ ምምሕዳር መልሚሉ ርኢቶ ካቢኔ ግዝያዊ ምምሕዳርን ህዝብን ተቐቢሉ ንዋና ኣመሓዳሪ ዞባን ኮሚቴ ምምሕዳር ዞባን ይሸይምን የልዕልን።

ለ. ርእሰ ምምሕዳር መልሚሉ ርኢቶ ካቢኔ ግዝያዊ ምምሕዳር፣ ህዝብን ቤት ምኽርን ተቐቢሉ ንከንቲባ፣ ምክትል ከንቲባን ኮሚቴ ከንቲባን ምምሕዳር ከተማ መቐለ ይሸይምን የልዕልን።

ሐ. ብዋና ኣመሓዳሪ ዞባ ዝምራሕ ኮሚቴ ምምሕዳር ዞባ ወይ ብከንቲባ ዝምራሕ ኮሚቴ ከንቲባ ምምሕዳር ከተማ መቐለ ምስ ርእሰ ምምሕዳር ብምምኽኻር ናይ ህዝብን ቤት ምኽርን ርኢቶ ተቐቢሎም ንከንቲባን ምክትል ከንቲባን ከተማ፣ ንዋና ኣመሓዳርን ምክትል ኣመሓዳርን ወረዳ ወይ ክ/ከተማ ሓዊሱ ኣባላት ኮሚቴ ፈፃሚ ስራሕ ወይ ኮሚቴ ከንቲባ ይሸ,ምን የልዕልን።

መ. ኮሚቴ ፈፃሚ ስራሕ ብዋና ኣመሓዳሪ ወረዳ ወይ ክፍለ ከተማ እናተመርሐ፤ ኮሚቴ ከንቲባ ብከንቲባ ከተማ እናተመርሐ ናይ ህዝብን ቤት ምኽርን ጣብያ ርኢቶ ብምቕባል ንዋና ኣመሓዳሪ፣ ምክትል ኣመሓዳርን ኣባላት

3. በዚህ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም፡-

ሀ. ርእሰ መስተዳደሩ መልምሎ የግዝያዊ አስተዳድር ካቢኔና የሕዝብ አስተያየት በመቀበል የዞን ዋና አስተዳዳሪ እና የዞን አስተዳደር ኮሚቴ ይሾማል፣ ያነሳል፣

ለ. ርእሰ መስተዳደሩ መልምሎ የግዝያዊ አስተዳደሩ ካቢኔ፣ የሕዝብ እና የምክርቤት አስተያየት በመቀበል የመቐለ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ፣ምክትል ከንቲባና የከንቲባ ኮሚቴ ይሾማል፣ ያነሳል፣

ሐ. በዞኑ ዋና አስተዳዳሪ የሚመራ የዞኑ አስተዳደር ኮሚቴ ወይም በከንቲባው የሚመራ የመቐለ ከተማ አስተዳደር የከንቲባ ኮሚቴ ከርእሰ መስተዳድሩ ጋር በመመካከር የሕዝብ እና የምክርቤት አስተያየት በመቀበል የከተማ ከንቲባ እና ምክትል ከንቲባ፣ የወረዳ ወይ ክ/ከተማ ዋና አስተዳዳሪው እና ምክትል ዋና አስተዳደሩን ጨምሮ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ወይም የከንቲባ ኮሚቴ አባላትን ይሾማል፣ ያነሳል

መ. የወረዳ ወይም የክፍለ ከተማ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በዋና አስተዳደሩ እየተመራ፣ የከተማ ከንቲባ ኮሚቴ በከንቲባው እየተመራ የሕዝብ እና የምክርቤት አስተያየት በመቀበል የቀበሌ ዋና አስተዳዳሪ፣ ምክትል ዋና አስተዳዳሪ

Tigray Regional State Interim Administration

ፈፃሚ ስራሕ ጣብያ ይሸምን የልዕልን።

ረ. ኣብዚ ዓንቀፅ ርኢቶ ቤት ምኽሪ ኣብ ዘድልዮም ጉዳያት ቤት ምኽሪ ርኢቶ ክሀብ ካብ ዝቐረበሉ ዕለት ጀሚሩ ኣብ ውሽጢ 7/ሸውዓተ/ ናይ ስራሕ መዓልትታት ርኢቶ እንተዘይኣቕሪቡ ናብ ዝቕፅል ስነስርዓት ይስግር፣

ሰ. ንኣፈፃፅማ እዚ ንኡስ ዓንቀፅ ስልጣን ብዝተውሃቦ ኣካል ዝካየድ ምልመላ ናይ ተመልማሊ ናይ ስራሕ ኣፈፃፅማ፣ ናይ ትምህርቲ ድልውነት፣ ዘለዎ ስነምግባርን ተቐባልነት ህዝብን ብኣግባቡ ተራእዩ ዝካየድ ይኸውን።

ሸ. በዚ ደንቢ እዚ መሰረት ኣብ ዝተፈላለዩ ብርኪታት ኣብ ዝካየዱ ናይ ምሽም ተግባራት ክንዲ ዝተኽኣለ ናይ ዝተፈላለዩ ውድባት ፖለቲካ፣ ደቂኣንስትዮን መናእሰይን ሚዛናዊ ተዋፅኦ ብዘረጋግፅ ኣግባብ ክካየዱ ኣለዎም፣

ቀ. ኣብዚ ንኡስ ኣንቀፅ እዚ ንዝተገለፀ ርኢቶ ህዝቢ ብዝምልከት ዝርዝር መምርሒ ኣፈፃፅማ ብርእሰ ምምሕዳር ይወፅእ

በ. ቤት ምኽሪ እምነት ኣብ ዝሰኣነሎም ዋና ኣመሓዳሪ፣ ምክትል ኣመሓዳሪ፣ ክንቲባ፣ ምክትል ክንቲባን ኮሚቴ ፈፃሚ ስራሕን ከም ኣግባብነቱ ንርእሰ

እና የቀበሌው ሥራ አስፈፃሚ አባላትን ይሾማል፣ ያነሳል፡

ረ. በዚህ ዓንቀፅ የምክር ቤት አስተያየት በሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ምክር ቤቱ አስተያየት እንዲሰጥበት ከቀረበለት ቀን ጀምሮ በ 7/ሰባት/ የሥራ ቀናቶች ውስጥ አስተያየት ካላቀረበ ወደ ቀጣዩ ስነስርዓት ይሻገራል፣

ሰ. ለዚህ ንኡስ ዓንቀፅ አፈፃፀም ስልጣን በተሰጠው አካል የሚካሄድ ምልመላ የተመልማዩ የስራ አፈፃፀም፣ የትምህርት ዝግጁነት፣ ያለው ስነምግባርና የህዝብ ተቀባይነት በአግባቡ ታይቶ የሚካሄድ ይሆናል።

ሸ. በዚህ ደንብ መሰረት በተለያዩ ደረጃዎች በሚካሄዱ የመሾም ስራዎች በተቻለ መጠን የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሴቶችና የወጣቶች ሚዛናዊ ተዋፅኦ በሚያረጋግጥ አኳኋን መካሄድ አለባቸው፣

ቀ. በዚህ ንኡስ ዓንቀፅ ለተገለፀው የህዝብ አስተያየት በተመለከተ በርእሰ መስተዳድሩ ዝርዝር የአፈፃፀም መመርያ ይወጣል

በ. ምክር ቤቱ እምነት ባጣባቸው ዋና አስተዳዳሪ፣ ምክትል አስተዳዳሪ ፣ ከንቲባ እና ምክትል ከንቲባ እንዲሁም የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እንደ አግባብነቱ ለርእሰ

ምምሕዳር ወይ ዞባ ምምሕዳር ውሳነ ሓሳብ ከቕርቡ ይኽእሉ።

ተ. ርእሰ ምምሕዳር ኣብ ምምሕዳር ከተማ መቐለ፣ ከተማ፣ ክፋል ከተማን ወረዳን ኣብ ምዕዳቕ፣ ምትሕልላፍን ኣጠቓቕማን በጀት ጥቡቕ ቁፅፅርን ክትትልን ክገበር ንዋና ኦዲተር ክእዝዝን ዋና ኦዲተር ብዘቕርቦ ርኽብ ኦዲት መሰረት ድማ ኣድላዪ ገደባትን ክልከላታትን ክገብር ይኽእል።

## ዓንቀፅ 7. ምጥንኻር ኣብያተ ምኽሪ-

ኣብያተ ምኽሪ ኣብ ምጥንኻር ብኣግባቡ ናይ ህዝቢ ድምፂ ወከልቲ ኮይኖን ውሽጣዊ ኣሰራርሓአን ብመትከል ግልፅነትን ተሓታትነትን ክምራሕ ብሕጊ መሰረት ኣድላዪ ደገፍን ክትትልን ክገብር ንኣማኻሪ ካውንስል ብሕጊ ዝተውሃቦ ስራሕን ሓላፍነትን ከምዘሎ ኮይኑ፦

1. ካቢኔ ግዝያዊ ምምሕዳር ካብ ኩሎም ክፋላት እቲ ካቢኔ ዘጣየሹ ኣካላት ዝተውፃእ ካብ 3-5 ኣባላት ዘለውዎ ናይ ኣብያተ ምኽርን ፈፀምቲ ኣካላትን ኣፈፃፅማ ስራሕትን ዝካየዱ ሽመትን ምልዓልን ዝከታተል ኮሚቴ ክጣየሽ ይኽእል።ነዚ ዝመርሕን ዘተሓባብርን ኣካልውን ብርእሰ ምምሕዳር ክምደብ ይኽእል።

መስተዳደሩ ወይም ለዞን አስተዳደሩ የውሳኔ ሐሳብ ሊያቀርቡ ይችላሉ፣

ተ. ርእሰ መስተዳደሩ በመቐለ ከተማ ፣ወረዳ፣ ከተማ እና ክፍለ ከተማ መስተዳደር በበጀት ማፅደቅ፣ ማስተላለፍና አጠቃቀም ጥብቅ ቁጥጥር እና ክትትል እንዲያደርግ ለዋና ኦዲተር ትእዛዝ ሊሰጥ እና ዋና ኦዲተሩ በሚያቀርበው የኦዲት ግኝት መሰረት አስፈላጊውን ገደቦች እና ክልከላዎች ሊያደርግ ይችላል፣

## ዓንቀፅ 7.ምክር ቤቶችን ስለማጠናከር፡-

ምክር ቤቶች በማጠናከር በአግባቡ የህዝብ ድምፅ ወኪሎች በመሆን ውስጣዊ አሰራራቸውን በግልፅኝነትና ተጠያቂነትን መርህ እንዲመራ በሕግ መሰረት አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል እንዲያደርግ ለአማካሪ ካውንስል በሕግ የተሰጠውን ስራና ሓላፊነት እንዳለ ሁኖ፦

1) የግዝያዊ አስተዳደር ካቢኔ ከሁሉም ካቢኔ ካቋቋሙ አካላት የተውጣጣ ከ3-5 አባላት የያዘ የምክር ቤቶች እና አስፈፃሚ አካላት የሥራ አፈፃፀም እና የሚካሄዱ የመሾምና የማንሳት ሥራዎች የሚከታተል ኮሚቴ ሊያቋቁም ይችላል። ርእሰ መስተዳድሩም ይህንኑ ተግባር የሚመራና የሚያስተባብር አካል ሊመድብ ይችላል።

Tigray Regional State Interim Administration

2. ኣባላት ኣብያተ ምኽሪ ወረዳ፣ ከተማን ክፍለ ከተማን ከከም በዝሒ ህዝበን ቁፅርም ካብ 150-201 ይኾኑ። ኣብ ምምሕዳር ከተማ መቐለ ድማ ካብ 300 ዘይነኣስ ኣባላት ይህልዉ።

3. ዝተጓደሉ ወይ ዘይተማልኡ ኣባላት ቤትምኽሪ ንምምላእ ሓጀፉይ ብዝኾነ ኣግባብ ብቐጥታ ናይ ህዝቢ ተሳትፎ ብዝካየድ መስርሕ ይኸውን።

4. ዝተጓደሉ ወይ ዘይተማልኡ ኣባላት ቤትምኽሪ ዝማልኡሉ ከይዲ፦

ሀ. ሕድሕድ ጣብያ ልዕሊ 18 ዓመት ዕድመኦም ዝኾኑ ነበርቲ ብዘካይድዎ ኣኼባ ናይ ምምሕዳር ከተማ መቐለ፣ ወረዳ፣ ከተማ፣ ክፍለ ከተማን ጣብያን ቤትምኽሪ ኣባላት ይውክሉ።

ለ. ንኣፈፃፅማ እዚ ንኡስ ዓንቀፅ እዚ ንኹሎም ነበርቲ ብዝባፃሕን ብዝሰማዕን ኣግባብ ዕላዊ ፃውዒት ተገይሩ ብዝተረኽበ ነበርቲ ይካየድ።

ሐ. ንዝርዝር ኣፈፃፅማ እዚ ከይዲ ዝርዝር መምርሒ ብርእሰ ምምሕዳር ይወፅእ።

**ዓንቀፅ 8. ናይ ምፍፃም ግቡእ፦**

1. በቢብርኪ ዝርከብ መሓውር መንግስቲ ሰራሕቲ መንግስቲ ብሕጊ፣ ስርዓትን

2) የወረዳ፣ ከተማና ክፍለ ከተማ የምክር ቤት አባላት እንደ ሕዝቡ ብዛት ቁጥራቸው ከ150-201 ይሆናሉ። በመቐለ ከተማ አስተዳደርም ከ300 ያላነሱ አባላት ይኖራሉ።

3) የተጓደሉ ወይም ያልተሟሉ የምክር ቤት አባሎች ለሟሟላት አካታች በሆነ አግባብ በቀጥታ የሕዝብ ተሳትፎ በሚካሄድ ስርአት ይሆናል።

4) የተጓደሉ ወይም ያልተሟሉ የምክር ቤት አባላት የሚሟሉበት አሰራር፦

ሀ. እያንዳንዱ ቀበሌ እድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ የሆኑ ነዋሪዎች በሚያካሂዱት ስብሰባ የመቐለ ከተማ አስተዳደር፣ ወረዳ፣ ከተማ፣ ክፍለ ከተማ እና የቀበሌ የምክር ቤት አባላት ይወክላሉ።

ለ. ለዚህ ንኡስ ዓንቀፅ አፈፃፀም ሲባል ለሁሉም ነዋሪዎች በሚዳረስ እና ሊሰማ በሚችል አግባብ ግልፅ ጥሪ ተደርጎ በተገኙ ነዋሪዎች ይካሄዳል።

ሐ. የዚህ ሂደት አፈፃፀም የሚመራበት ዝርዝር መመርያ በርእሰ መስተዳደሩ ይወጣል።

**ዓንቀፅ 8. የመፈፀም ግዴታ**

1. በየደረጃው የሚገኝ የመንግስት መዋቅር የመንግስት ሥራዎች በሕግና፣ ስርዓትና

Tigray Regional State Interim Administration

ትልምን ናይ ምፍፃም ግቡእ ኣለዎ።

2. በቢብርኩ ዝርከቡ መሓውራት መንግስቲ ብልዕሊኦም ብዘሎ መንግስታዊ መሓውርን ኣመራርሓን ዝወሃብዎም መደባትን መምርሒታትን ናይ ምፍፃምን ክፍፀሙ ናይ ምግባርን ግቡእን ሓላፍነትን ይህልዎም።

በተቀመጠው ዕቅድ መሰረት የመፈፀም ግዴታ አላቸው።

2. በየደረጃው የሚገኙ የመንግስት መዋቅር ከበላይ አካል የመንግስት መዋቅር እና አመራር የተሰጣቸው ሥራዎች እና መምሪያዎችን የመፈፀም እና እንዲፈፀሙ የማድረግ ግዴታ እና ሓላፊነት አላቸው።

**ዓንቀፅ 9. ግቡእ ምትሕብባር፦**

ንኣፈፃፅማ እዚ ደንብን ነዚ ደንቢ ንምፍፃም ዝወፁ መምርሕታትን ኣሰራርሓታትን ዝኾነ ሰብ ክተሓባበር ግቡእ ኣለዎ።

**ዓንቀፅ 9. የመተባበር ግዴታ፦**

ለዚህ ደንብና ይህንን ደንብ ለማስፈፀም ለሚወጡ መምሪያዎች እና አሰራሮች አፈፃፀም ማንኛውም ሰው የመተባበር ግዴታ አለው።

**ዓንቀፅ 10. ተሓታትነት**

እዚ ደንቢ ኣዚ ብምትሕልላፍ ዝፍፀም ዝኾነ ይኹን ተግባር ኣግባብነት ብዘለዎም ሕግታት ገበን ተሓታትነት የስዕብ።

**ዓንቀፅ 10.ተጠያቂነት፦**

ይህ ደንብ በመተላለፍ የሚፈፀም ማንኛውም ተግባር አግባብነት ባላቸው ሕጎች የወንጀል ተጠያቂነት ያስከትላል።

**ዓንቀፅ 11. ተፈፃምነት ዘይብሎም ሕግታት፦**

ነዚ ደንቢ ዝፃባእ ሕግን ልማዳዊ ኣሰራርሓን ኣብዚ ደንቢ ኣብ ዝተሸፈነ ዋኒን ተፈፃምነት የብሉን።

**ዓንቀፅ 11.ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች፦**

ይህንን ደንብ የሚቃረን ሕግ እና ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈነ ጉዳይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

ግዚያዊ ምምሕዳር ክልል ትግራይ
Tigray Regional State
Interim Administration



CamScanner

## ዓንቀፅ 12. መሰጋገሪ ድንጋገ

እዚ ደንቢ ቅድሚ ምውፅኡ ዝተፈፀመ ወይ ዝተውሃበ ውሳነ ነዚ ደንቢ ዝፃባእ ክሳብ ዘይኮነ ዝፀንዐ ይኸውን። እንተኾነ ግን እዚ ደንቢ ቅድሚ ምውፅኡ ኣብ ስራሕ ዝፀንሑ በቢብርኩ ዝርከቡ ሓለፍቲ ስራሕ ከም ብሓድሽ ምትዕርራይ ከየድለየ በዚ ደንቢ እዚ ናይ ምሻም ስልጣን ዘለዎ ኣካል እንተኣሚኑሎም ኣብዘለዉዎ ሓላፍነት ስራሕ ይቕፅሉ።

## ዓንቀፅ 13. ተፈፃምነት እዚ ደንቢ

እዚ ደንቢ ብካቢኔ ግዚያዊ ምምሕዳር ትግራይ ካብ ዝፀደቐሉ ካብ ዕለት 12/05/2017 ዓ/ም ጀሚሩ ተፈፃሚ ይኸውን።

ጌታቸው ረዳ ካሕሳይ

ፕረዚደንት ግዝያዊ ምምሕዳር ክልል ትግራይ

<u>መቐለ</u>

## ዓንቀፅ 12 የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት የተፈፀመ ወይም የተሰጠ ውሳኔ ይህንን ደንብ የሚቃረን እስካልሆነ ድረስ የፀና ይሆናል። ሆኖም ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት በየደረጃው ስራ ላይ የነበሩ የስራ ሓላፊዎች መልሶ ማደራጀት ሳያስፈልግ በዚህ ደንብ መሰረት የመሾም ስልጣን ባለው አካል ከታመነባቸው ባሉበት የስራ ሓላፊነት እንዲቀጥሉ ይደረጋል።

## ዓንቀፅ 13. የዚህ ደንብ ተፈፃሚነት

ይህ ደንብ በትግራይ ክልል ግዚያዊ መስተዳደር ካቢኔ ከፀደቀበት ቀን 12/05/2017 ዓ/ም ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል።

ጌታቸው ረዳ ካሕሳይ

የትግራይ ክልል ግዚያዊ አስተዳደር ፕሬዚደንት

<u>መቐለ</u>

Tigray Regional State Interim Administration